## የኢት/ካ/ቤተ/ክ ሚሌኒየም/ኢዮቤልዩ ክብረ በዓል ሚያዝያ 26/2000 ዓ.ም. መካኒሳ በሚገኘው ዶን ቦስኮ ረዳኢተ ክርስቲያን ማርያም ቤ/ክ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከበረ

በበዓሉ ላይ የኢት/ካ/ቤ/ክ ብፁዓን ጳጳሳት፣ የቅ. መንበር እንደራሴ፣ የተለያዩ ሃይማኖት አባቶች የኢት/ መንግሥስት ከፍተኛ ባለሥልጣናት፣ አምባሳደሮች፣ ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ መዕመናን፣ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መላው የአ.አ. ከተማ ካቶሊካውያን፣ በጐ ፈቃድ ያላቸው ወገኖች ተገኝተዋል:: በአጠቃላይ ከ6ሺ.ህ ሰው በላይ በበዓሉ ላይ መገኘታቸውን ለማወቅ ተችሏል::

የበዓሉ ሥነ ሥርዓት በብፁዕ አቡነ ተስፋስላሴ የአዲግራ ሀ/ስ ጳጳስና የኢ/ካ/ቤ/ክ የኢዮቤልዩ ክብረበዓል አዘጋጅ ሰብሳቢ በስፍራው የተገኙትን ሁሉ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ምስጋና አቅርበዋል::

በኢዮቤልዩ ዓመት የተለያዩ መንፈሳዊ መርሃ ግብሮች እየተደረጉ መሆናቸውንና ከስጦታዎች ሁሉ ታላቅ ስጦታ የሆነውን የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም ለማክበርና ቃል ኪዳናችንን ከአምላካችን ጋር የምናጠናክርበት ዕድል በማግኘታችን ክብር ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን በማለት ምስጋና አቅርበዋል::

በመቀጠልም ብፁዕ አቡነ ራሜሮ ሞሊነር የቅ. መንበር እንደራሴ የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ቤኔደክቶስ ልዩ መልዕክተኛ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን የብፁዕ ካርዲናል ኢቫን ዲያስ የውክልና ደብዳቤ በንባብ ያሰሙ ሲሆን የኢትዮጰያ ቤተክርስቲያን ለቅዱስ ቁርባን ክብር ፀሎት ከመላው ዓለም በረከት እንደሆነ ገልፀዋል::

የቅዳሴ ሥነ ሥርዓቱ በብፁዕ አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያንና በብፁአን ጳጳሳት የተመራ ሲሆን ብፁዕ ካርዲናል ኢቫን ዲያስ በስፍራው ለተሰበሰበው ምዕመን ቃለ መዕዳን አሰምተዋል:: በዚህም ወቅት ክር.ሊ.ጳ. ቤኔዲክቶስ 16ኛ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በስጦታ የተላከውን ጽዋ ለብፁዕ አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ አበርክተዋል::

የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት እንዳለቀ ብፁዕ አቡነ ተስፋ ስላሴ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት እንዲሁም በጐ ፈቃድ ላለቸው ወገኖች የኢት/ካ/ቤ/ክ መልዕክት አስተላልፈዋል::

በመጠቀልም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚሌኒየም አከባበር ጽ/ቤት ዋና ሃላፊ አቶ ስዩም በረደድ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እያደረገች ያለውን የልማት ሥራ በማድነቅ እንደትናንቱ ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕድገት ከሌሎች ወገኖች ጋር በመተባበር አጠናክራ እንደምትቀጥል ያላቸውን ምኞት ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በብፁዕ አቡነ ብርሃነ ኢየሱስ አቅራቢነት በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ለረጅም ዓመታት አገልግሎት የሰጡ ካህናትና ምዕመናን ከብፁዕ ወቅ/ር/ሊ/ጳ ቤኔዲክቶስ 16ኛ የተለከ የክብር ኒሻንና ከፍተኛ የክብር የምስክር ወረቀት

ለክቡር አባ ገብረማርያም አመንቴ
ለክቡር አባ ኪዳነማርያም ገብራይ
ለክርት ሲ/ር ብርጅድ
ለክቡር ጀኔራል ወልደስላሴ በረካ ከነባለቤታቸው
ለክብርት ወ/ሮ ደብሪቱ አሥራት

በብፁዕ ካርዲናል ኢቫን ዲያስ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢዮቤልዩ ክብረ በዓል አከባበር አስተባባሪ ኮሚሽን ለብፁዕ ካርዲናል ኢቫን ዲያስና ለብፁዕ ወቅ/ር/ሊ/ጳ ቤኔዲክቶስ 16ኛ የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ መስቀሎች የያዙ ስጦታዎች በኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ስም ያበረከቱላቸው ሲሆን በመጨረሻም ብፁዕ ካርዲናል ኢቫን ዲያስ ከብፁዓን የኢት/ካ/ጳጳሳት ጋር በመሆን የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትን ልዩ ቡራኬ በመስጠት የበዓሉ ሥነ ሥርዓት ፍፃሜ ሆኗል፡፡

በዓሉን ልዩ የሚያደርገው የሕዝቡ ብዛት ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ የአየር ንብረት የበልግ ዝናም ባለመገኘቱ የሕዝቡ ዋና ጭንቀት የነበረ ሲሆን በበዓሉ ዕለት ከማለዳው 10:00 የጀመረው ዝናም የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት ሊጀመር ተኩል ሰዓት ሲቀረው በመቆሙ ቅዳሴው የተጀመረ ሲሆን በቅዱስ ቁርባን ሥነ ሥርዓት ጊዜ የጀመረወ ሃይለኛ ዝናም የበዓሉን ገጽታ አላደበዘዘወም፡፡ የበለጠ ምዕመናኑ እግዚአብሔር ፀሎታችንን ሰማልን በማለት ምስጋና በማቅረብ እስከ መጨረሻ ሥነ ሥርዓቱን በደስታ ተከታትሎታል፡፡

ብፁዕ ካርዲናል ኢቫን ዲያስ የሥራ ጉብኝታቸውን ፈጽመው ሚያዝያ 27 ለሥራ ጉብኝት ወደጅቡቲ አምርተዋል፡፡